# አዋጅ ቁጥር -------------፪ሺ፲፰ ዓ.ም

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የሚሊሻ ኮሚሽን ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ

## ➢ የአዋጁ አስፈላጊነት

ለፌደራሉም ሆነ ለክልሉ ሕገ-መንግሥትና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ታማኝ፣ ታዛዥና ተገዥ የሆነ፣ የተጣለበትን ሕገ-መንግሥታዊ ተልዕኮ በብቃት መወጣት የሚችልና የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ባደረገ መልኩ ተልዕኮዉን የሚፈጽምና የሚመራ የሚሊሻ እና የሰላም አስከባሪ ሃይል ማደራጀት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከዚህ በፊት በተበታተነ ሁኔታ በሥራ ላይ ያሉትን የሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፫/፩ሺ፱፻፹፰ እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፹፩/፩ሺ፱፻፺፩ን በአንድ የሕግ ማዕቀፍ በማጠቃለል በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ እና የተቋሙን አደረጃጀት ከሚሰጠዉ ሰፊ አገልግሎት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ በማስፈለጉ፤

እነዚህ አዋጆች ሥራ ላይ ከዋሉ ረጅም ዓመታትን ያስቆጠሩ በመሆናቸው የተፈጠሩ አዳዲስ ክልላዊ ዕድገቶችን፣ አዳጊ ፍላጎቶችን፣ የአገራችንና የክልላችንን እንዲሁም ቀጠናዊ ሁኔታዎችንና የወደፊት አዝማሚያዎችን ግምት ውስጥ ያስገባ የሕግ ማዕቀፍ መኖርን የሚጠይቅ በመሆኑ፤

የኮሚሽኑ አመራሮችና ባለሙያዎች የጡረታ ዕድሜን፣ የሰላም አስከባሪና ሚሊሻ አባላት ደግሞ የአገልግሎት ዘመን፣ ጥቅማጥቅሞች፣ ማበረታቻዎችና ሽልማቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮች በሕግ ማዕቀፍ ምላሽ ሊያገኙ እንደሚገባ በመታመኑ፤

## በረቂቅ አዋጁ የዝግጅት ሂደት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

1. አዋጁን ለማዘጋጀት የተቋሙ የተለያዩ የቀድሞ አዋጅና ደንቦችን ፣ የተለያዩ የፀጥታ ተቋማት አዋጆችና ደንቦችን ታሳቢ ተደርጎ የተዘጋጀ መሆኑ
2. በተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ላይ የተቋሙ ባለድርሻ አካላት የተሳተፉ መሆኑ ፡ - ለምሳሌ ፡- የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮችና ባለሙያዎች ፣
3. በተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ላይ የዞን እና የወረዳ አመራሮችና ባለሙያዎች ፣

4. በዚሁ ረቂቅ አዋጅ ላይ የክልሉ ሰላምና ፀጥታ ቢሮ አመራሮችና ባለሙያዎች ፣
5. የክልሉ ፍትህ ቢሮ አመራሮችና የህግ ባለሙያዎች
6. በረቂቅ አዋጁ ላይ አዋጅ የርዕሰ መስተዳድሩ የህግ አማካሪ
7. ረቂቅ አዋጁ በተለያዩ ባልድርሻ አካላት ሰፊ ውይይት እየተደረገበትና በውይይቱ እየዳበረ ከመጣ በኋላ የክልል አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በሰፊው መክሮበታል
8. በመጨረሻም የአማራ ክልል ምክር ቤት የህግና ፍትህ አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መክሮበታል ፡፡ በመሆኑም ፡-

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፱ ንዑስ አንቀጽ ፫ (፩) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ረቂቅ አዋጅ አዋጅ አድርጎ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌ

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የተሻሻለው የሚሊሺያ ኮሚሽን ማቋቋሚያ፣ ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ------------- /፪ሺ፲፰ ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"ቢሮ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ነው፤

፪/ **"ኮሚሽን ወይም "ኮሚሽነር** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሚሊሻ ኮሚሽን ወይም የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ነው፤፤

፫/ **"ዋና መምሪያ እና ዋና መምሪያ ኃላፊ"** ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው በኮሚሽኑ ስር በሚገኙ የስራ ክፍሎች ወታደራዊ ጠባይ ያላቸው ከፍተኛ የሥራ መደቦች እና በዚሁ የሥራ መደብ ላይ ተመድቦ በኃላፊነት የሚሠራ ሰው ነው፤

፬/ **"መምሪያ"** እና **"መምሪያ ኃላፊ"** ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው በኮሚሽኑ ሥር በሚገኙ ዞኖች እና በዞን ደረጃ በተዋቀሩ ከተማ አስተዳደሮች የተዋቀረ መምሪያ እና የዚሁ መምሪያ ኃላፊ ነው፤

፭/ **"ጽሕፈት ቤት"**ማለት የወረዳ ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ወይም የከተማ አስተዳደር ክፍለ ከተማ ሚሊሻ ጽህፈት ቤት ማለት ነው፤

፮/ **"ዋና ክፍል"** እና **"ዋና ክፍል ኃላፊ"** ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው በኮሚሽኑ ውስጥ ወታደራዊ ጠባይ ያላቸው ከዋና መምሪያ ቀጥሎ እና ከዞን መምሪያ ቀጥሎ ያሉ ከፍተኛ የሥራ መደቦች እና በዚሁ የሥራ መደብ ላይ ተመድቦ በኃላፊነት የሚሠራ ሰው ነው፤

፯/ **"ክፍል"** እና **"ክፍል ኃላፊ"** ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው በኮሚሽኑ ሥር በሚገኙ ዞኖች ወይም በዞን ደረጃ በተዋቀሩ ከተማ አስተዳደሮች ስር ለተደራጁ ወረዳ ሚሊሻ ጽሕፈት ቤቶች እና ክፍለ ከተማ ሚሊሻ ጽ/ቤቶች ወታደራዊ ጠባይ ያላቸዉ ከፍተኛ የሥራ መደቦች እና በዚሁ የስራ መደብ ላይ ተመድቦ በኃላፊነት የሚሠራ ሰው ነው፤

፰/ **"የኮሚሽን አመራር"** ማለት በተዋረድ የተደራጀ እና ወታደራዊ ጠባይ ባላቸው ወይም በሲቪል የሥራ መደቦች በየትኛዉም የአደረጃጀት ዕርከን ተመድቦ ወይም በኃላፊነት የሚሠራ ሰው ነው፤

፱/ **"ባለሙያ"** ማለት መሠረታዊ የሚሊሻ ሥልጠና አጠናቆ ቃለ - መሃላና የቅጥር ውል ፈጽሞ እንደማንኛውም መለዮ ለባሽ ሙሉ መብቱ ተጠብቆ በየትኛውም ደረጃ በኮሚሽኑ ውስጥ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ደመወዝተኛ ሠራተኛ ነው፤

፲/ **"መለዮ ለባሽ"** ማለት የሚያስፈልገውን የሚሊሻ ስልጠና የወሰደ እና ሚሊተሪ ሆኖ የተመደበ ማንኛውንም ጥቅማ ጥቅም የሚያገኝ ደመወዝተኛ ሰው ነው፤

፲፩/ **"የሚሊሻ ቀጠና አስተባባሪ"** ማለት በቀጠና ደረጃ ተመድቦ የሰላም አስከባሪና የቀበሌ ሚሊሻን በኃላፊነት የሚመራ ደመወዝተኛ ሠራተኛ ነው፤

፲፪/ **"ሰላም አስከባሪ"** ማለት ከልማት ተግባሩ ሳይለይ ከሚሊሻው መካከል የተሻለ ብቃት ያላቸውን በመመልመልና ተጨማሪ የሰላም አስከባሪነት ሥልጠና ወስዶ፣ በወታደራዊ አደረጃጀት ውስጥ ታቅፎ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ለጸጥታ ስራ በሚሰማራበት ወቅት ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም እየተከፈለው ሕግ ለማስከበር ቅድሚያ ስምሪት የሚወስድና አገልግሎት ለመስጠት የፈቀደ ሰው ነው፤

፲፫/ " **የሚሊሻ አባል** " ማለት ከመደበኛ ሥራው ወይም ከልማት ተግባሩ ሳይነጠል በመንግሥት ወይም በግሉ በታጠቀው የጦር መሣሪያ ወይም ያለ ጦር መሣሪያ የአካባቢውን ሰላምና ጸጥታ ለማስከበር በማሕበረሰቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ተመልምሎ፣

መሠረታዊ የሚሊሻነት ሥልጠና ወስዶ ፣ በሚሊሻ አደረጃጀት ውስጥ ታቅፎ ፣ ምንም ዓይነት ደመወዝ ሳይከፈለው የሚሊሻነት አገልግሎት ለመስጠት የፈቀደ ሰው ነው፤

፲፬/ "**አደረጃጀት**" ማለት የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባላት በክፍለ ጦር ፣ በሻለቃ፤ በሻንበል፤ በመቶ እና በጓድ ተደራጅቶ በዕዝ የሚመራ የወታደራዊ አደረጃጀት ነው፤

፲፭/ "**ግዳጅ**" ማለት ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር ፣ ባለሙያ ፣ የሰላም አስከባሪ ወይም የሚሊሻ አባል መሠረታዊ የሚሊሻነት ሥልጠና ወስዶ ቃለ - መሃላ ከፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ በማንኛውም ምክንያት እስከሚሰናበትበት ጊዜ ድረስ በተናጠል ወይም ከፌዴራልና ከክልል የጸጥታ ኃይሎች ጋር በጥምረት የሚያከናውነው ማንኛውም ዓይነት አካባቢያዊ ፣ ክልላዊና ሃገራዊ ይዘት ያለው የስምሪት ተግባር ነው፤

፲፮/ "**በክብር የተሰናበተ**" ማለት የትኛውም ዓይነት የዲስፕሊን ጉድለት ሳይኖርበት ተልዕኮውን በአግባቡ ተወጥቶ በዚህ አዋጅ ወይም አግባብነት ባለው ደንብና መመሪያ መሠረት የተሰናበተ ሰው ነው፤

፲፯/ "**የጸጥታ ተቋም**" ማለት የሃገር መከላከያ ሰራዊት፣ የፌዴራል ፖሊስ፣ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ የክልሉ ሰላምና ፀጥታ ፣ የክልል ፖሊስ፣ የማረሚያ ቤት ፖሊስ እና የክልሉን የሚሊሻ ኮሚሽን የሚመለከት ነው፤

፲፰/ "**የጦር መሣሪያ አስተዳደር**" ማለት በክልሉ ውስጥ የጦር መሣሪያ ለሚያስፈልጋቸው የሰላም አስከባሪ፣ የሚሊሻ አባላት፣ የኮሚሽኑ አመራሮች የሰላም እና ፀጥታ አመራሮች ትጥቅ የማቅረብ፣ የማስታጠቅ፣ የትጥቅ ፈቃድ መታወቂያ የመስጠት፣ የማደስ፣ የመሰረዝ፣ የመዉረስ፣ አጠቃቀሙን የመከታተልና የመቆጣጠር ሂደት ነው፤

፲፱/ "**ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ**" ማለት በፌደራል የጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ መሠረት የጦር መሣሪያን በክልል ደረጃ እንዲያስተዳድር ስልጣን በተሰጠዉ አካል የፈቃድ ደብተር በሌለዉ ወይም በየዘመኑ የታደሰ የፈቃድ ደብተር ባልተሰጠዉ ግለሰብ ወይም ተቋም በትጥቅነት የተያዘ ማንኛውም ዓይነት የጦር መሣሪያ ነው፤

፳/ "**ሲቪል ሠራተኛ**" ማለት በኮሚሽኑ ውስጥ በሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት በሚተዳደሩ የሥራ መደቦች የተቀጠረ ሰው ነው፤

፳፩/ “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፪/ በዚህ አዋጅ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ያካትታል፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ፬. የአሠራር መርሆዎች

ኮሚሽኑ ሥራዎችን ሲሰራ የሚከተሉትን መርሆዎች መሠረት በማድረግ ይሆናል፦

፩/ ሰብዓዊ ክብር የተላበሰ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በዘር፣ በብሔር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካ ፣ በሐይማኖት ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሐብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ባለማድረግ፤

፪/ የቡድን አሠራር መርህን በመከተል የጋራና የግል ተጠያቂነትንና ኃላፊነትን መውሰድ፤

፫/ በታማኝነትና በቅንነት መርህ በመመስረት የተሰጠን ኃላፊነት መወጣት ፤

፬/ የአሳታፊነት፣ የተጠያቂነትና የግልጽነት መርህን መከተል ።

# ክፍል ሁለት

# ስለ ኮሚሽኑ መቋቋም፣ ሥልጣን፣ ተግባርና አደረጃጀት

## ፭. መቋቋምና ተጠሪነት

፩/ የአማራ ክልል ሚሊሺያ ኮሚሽን ”ከዚህ በኋላ “ ኮሚሽን ” እየተባለ የሚጠራ አካል በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፤

፪/ የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል፤

## ፮. ዋና መሥሪያ ቤት

፩/ የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት ባህርዳር ከተማ ይሆናል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ቢኖርም ኮሚሽኑ እስከ ቀበሌ ባለው የአስተዳደር ዕርከን ድረስ የተዘረጋ የአደረጃጀት መዋቅር ይኖረዋል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የኮሚሽኑ አደረጃጀት የአካባቢውን አቀማመጥ አመችነትና የጸጥታ ሁኔታ ግምት ውስጥ

በማስገባት ወታደራዊ የጦር ክፍል አደረጃጀት መርህን በመከተል በንዑስ ቀበሌ፣ በቀበሌ ፣ በቀጠና ወይም በክላስተር፣ በወረዳ፣ በዞን የተዋቀረ አደረጃጀት ሊኖረው ይችላል።

## ፮. ዓላማ

ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የሕዝቡን የነቃ ተሳትፎ በማረጋገጥ የክልሉን ሕገ - መንግሥትና ሕገ - መንግስታዊ ሥርዓት ከማንኛውም ዓይነት ስጋትና ጥቃት መከላከል፤

፪/ የክልሉን ህዝብ ሰላምና ደህንነት ፣ የሕዝብ የመንግሥት የልማት ተቋማትን ከማናቸውም ዓይነት ጥቃት መከላከል ፤

፫/ ለሕገ - መንግሥታዊ ሥርዓቱ ፍጹም ታማኝና ታዛዥ የሆነ፣ በጠንካራ የሥራ ባህልና ሥነ - ምግባር የታነጸ ፣ በሁሉም መስክ በሚኖርበት ማሕበረሰብ በአርአያነት የሚታይ የኮሚሽን አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ አባል መገንባት።

## ፯. የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባራት

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ከክልል ጀምሮ በተዋረድ የሚገኙ የኮሚሽኑን አስተዳደር መዋቅርን ይዘረጋል፤ ያደራጃል፤ ያስተባብራል፤ ይመራል፤

፪/ የህዝቡን የነቃ ተሳትፎ በማረጋገጥ የክልሉን ሕገ መንግሥት እና ሕገ - መንግሥታዊ ሥርዓት ከማንኛውም ዓይነት የፀረ ሰላም ኃይሎች ስጋትና ጥቃት ይከላከላል ፤

፫/ ሕግ ያስከብራል ፤ የመንግሥት ሕግና ፖሊሲዎችን ይፈጽማል ፤ ያስፈጽማል ፤

፬/ በየትኛውም የክልሉ አካባቢ የሚፈጠሩ ሕገወጥ ድርጊቶችን ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል ፣ ከሚመለከታቸው የጸጥታ አካላት ጋር በመሆን ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፭/ የተቋሙን አጠቃላይ የመፈጸም አቅም የመገንባትና ተጠብቆ እንዲቀጥል የማድረግ፣ አዳዲስ አቅሞችን የሚፈጥሩ ሥራዎችን ይሠራል፤

፮/ አጠቃላይ የኮሚሽኑን የሰው ኀይል ምልመላ፣ ሥልጠና፣ ግንባታ፣ አደረጃጀት፣ ትጥቅና ስምሪት ይወስናል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፤

፯/ የኮሚሽኑን አመራሮች፣ ባለሙያዎች፣ የሰላም አስከባሪውንና የሚሊሻውን ሃይል ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊና ሥነ-ልቦናዊ የግንባታ ሥራዎችን በልዩ ትኩረት ይመራል፤

፰/ ክልል አቀፍ ወይም በክላስተር የሚሊሻ ማሠልጠኛ ማዕከላትን ይገነባል፤ ያደራጃል፤ ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

፱/ የኮሚሽኑን መዋቅርና አጠቃላይ የሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ ሃይሉን ተልዕኮ የመወጣት ዝግጁነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የኢንስፔክሽን፣ የአመራር፣ የዕዝና ቁጥጥር ሥርዓትን ይዘረጋል፤ ይገነባል፤ ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል፤

፲/ ሚሊሻው እና ሰላም አስከባሪ ኃይሉ ለረጅም ጊዜ ከመደበኛ ተግባሩ ሳይነጠል በአካባቢው በሚካሄዱ ጸጥታ የማስከበር ስምሪቶችና በሌሎች መንግሥታዊ ሥራዎች ከሌሎች የጸጥታ አካላትና ሕዝብ ጋር ተቀናጅቶ የሚሠራበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፩/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሃገር ሰላምና ደህንነት መረጋገጥ ከሃገር መከላከያ ሰራዊት ጎን ይሰለፋል፤

፲፪/ የተቋሙን ጠቅላላ ኀብት፣ በጀት እና የሰው ኀይል ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤ ይመራል፤ ጥቅም ላይ ያውላል፤

፲፫/ በተሰጠው ህግ የማስከበር ስልጣን መሠረት ሕገ - ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውርን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ለሕግ እንዲቀርቡ ያደርጋል ፤

፲፬/ የኮሚሽኑ አመራሮች፣ ባለሙያዎች፣ ሰላም አስከባሪዎች፣ የሚሊሻ አባላት እና ሌሎች ሲቪል ሠራተኞች አግባብ ባለው ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈቀዱና የሚፈቀዱ ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን ጥናቶችን በማድረግ ሰንዶ ለቢሮው በማቅረብ በመንግስት ሲፈቀድ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፭/ በመለዮ ለባሽ ምልመላና ቅጥር፣ በትምህርትና ሥልጠና፣ በዕድገት አሰጣጥ፣ በስንብት፣ በደንብ ልብስ አለባበስና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ክልል አቀፍ ረቂቅ መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለቢሮው በማቅረብ በመስተዳድር ምክር ቤት ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፮/ ሚሊሻው እና ሰላም አስከባሪው በግዳጅ በተሰማራበት ወቅት ለሚደርስበት ጉዳት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ድጎማና ማበረታቻ እንዲያገኝ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን መረጃዎችን አደራጅቶ በመላክ እንዲከፈለው ያደርጋል፤

፲፯/ ለሥራው የሚያስፈልጉ የአስተዳደር ሠራተኞችን በክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፤

፲፰/ የተቋሙን ሰብዓዊና ቁሳዊ ኀብት ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ዘመናዊ የኀብት አስተዳደር ሥርዓቶችን በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፱/ የተቋሙን የመፈጸም ብቃት የሚያጎለብቱና መልካም ገጽታን የሚገነቡ ክልላዊና ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው ልዩ ልዩ ሥራዎችን ያከናውናል ፤

፳/ የኮሚሽኑን ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ያቀርባል ፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል ፤

፳፩/ ውሎችን ይዋዋላል ፤ የንብረት ባለቤት ይሆናል ፤ በስሙ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤

፳፪/ የኮሚሽኑ አመራርና ባለሙያ ፣ የሰላምና ፀጥታ ፣ ሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ አባል የታጠቀውን የጦር መሣሪያ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣ ያሰማራል፤

፳፫/ ሌሎች ከኮሚሽኑ ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሕጋዊ ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፱. <u>የኮሚሽኑ መዋቅራዊ አደረጃጀት</u>

**ኮሚሽኑ ፦**

፩/ የኮሚሽኑ ኮሚሽነርና ተጠሪነታቸው ለኮሚሽነሩ የሆኑ ምክትል ኮሚሽነሮች፤

፪/ ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎችና የሥራ ክፍል ኃላፊዎች፤

፫/ የኮሚሽኑ አመራሮች፣ ባለሙያዎች፣ ሰላም አስከባሪ፣ ሚሊሻ አባላት፣ እና

፬/ ሲቪል ሠራተኞች፤ ይኖሩታል፡፡

## ፲. <u>የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባራት</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ መሠረት ለኮሚሽኑ የተሰጡ ተግባራትን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ የሚከተሉት ተጨማሪ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) የኮሚሽን አመራሩን፣ ባለሙያውን፤ ሰላም አስከባሪውንና ሚሊሻ አባሉን ለሕገ-መንግሥቱና ሕገ - መንግሥታዊ ሥርዓቱ ታማኝ፣ ታዛዥና ተገዥ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ይህንን እምነት የሚፈጥሩና የሚያሳድጉ የአቅም ግንባታ ሥራዎች በቀጣይነት እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

ለ) መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ኮሚሽኑን ወክሎ ግንኙነት ያደርጋል፤

ሐ) የኮሚሽኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣ በክልሉ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ሥራ ላይ ያውላል፤ ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፤

ሠ) የኮሚሽኑን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ዘገባ በሚመለከት ለቢሮው እና ለክልሉ ገንዘብ ቢሮ ያቀርባል፤

ረ) የዞን መምሪያ ኃላፊዎችን ምደባ ፣ ዝውውር እና ከኃላፊነት ማንሳት ለቢሮው አቅርቦ እንዲፀድቅ ያደርጋል ፤

ሰ) በክልል ደረጃ ዋና መምሪያ ኃላፊዎችን፣ ዋና ክፍል ኃላፊዎችን፣ የዞን መምሪያ ዋና ክፍል ኃላፊዎችን እና የወረዳ ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ሃላፊዎችን ምደባ መርምሮ ያጸድቃል፣ ያዛውራል፣ ያነሳል፤

ሸ) በየደረጃው የሚገኙ የሚሊሻ ባለሙያዎች፣ የቀጠና አስተባባሪዎች፤ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባላት ምልመላ፣ ቅጥር፣ ዕድገት፣ አስተዳደርና ስንብት ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ መሠረት እንዲፈጸም ያደርጋል፤

ቀ) የሲቪል አስተዳደር ሠራተኞች ምልመላ፣ ቅጥር፣ ዲሲፕሊን፣ አስተዳደርና ስንብት በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

በ) በዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት ከሥራ የተሰናበቱ፣ ከኃላፊነት የተነሱ፣ የተዛወሩ መለዮ ለባሾች በሚያቀርቧቸዉ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ላይ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

ተ) ሌሎች ከሥልጣንና ኃላፊነቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፲፩. የምክትል ኮሚሽነሮች ሥልጣንና ተግባራት

፩/ ኮሚሽኑ ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝ መጠን ከአንድ በላይ ምክትል ኮሚሽነሮች የሚኖሩት ሆኖ ወታደራዊ፣ ሎጅስቲክሳዊና አስተዳደራዊ የሥራ ክፍሎችን ያስተባብራሉ፣ ይመራሉ፤

፪/ የኮሚሽኑን ሥራዎች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ያግዛሉ፤

፫/ ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ውክልና የተሰጠው ወይም በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ኮሚሽነሩ ኮሚሽነሩን ተክቶ ይሠራል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የተደነገገው ቢኖርም ሹመቱ በተመሳሳይ ቀን የተሰጠ ከሆነ ከተሿሚዎች መካከል ሴት ካለች ቅድሚያ ለሴት ይሰጣል፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ በተገለፀው መሠረት መለየት ካልተቻለ የበለጠ የስራ ልምድ ያለው የሚመራ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሦስት

# ስለ ኮሚሽኑ አመራሮች፣ ባለሙያዎች፣ ሰላም አስከባሪና ሚሊሻ አባላት አስተዳደር

## ፲፪. ስለ ምልመላና ምደባ

፩/ ኮሚሽኑ ለሰላም አስከባሪና ለሚሊሻነት ብቁና ፈቃደኛ የሆኑ፣ ቋሚ የቀበሌው ነዋሪ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ሰዎችን በሕዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ይመለምላል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ለኮሚሽኑ አመራርነት ወይም ባለሙያነት ብቁ የሆኑ ሰዎችን መልምሎ ይመድባል፤ የቅጥር ውል ይፈጽማል፤ ያስተዳድራል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

## ፲፫. ስለ ሥልጠና

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ አባል አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት መሠረታዊ የሚሊሺያነት ሥልጠና ይሰጠዋል፤

፪/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪ፣ የሚሊሻ አባል ለተመለመለበት ኃላፊነት ብቁ የሚያደርገው የአመራር ሥልጠና ይሰጠዋል፡፡

## ፲፬. ስለ ቃለ መሃላ

ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል ለተልዕኮ የሚያበቃውን ሥልጠና እንዳጠናቀቀ ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥሉ ማንኛውንም ህገ ወጥ ድርጊት በመከላከል በታማኝነት፣ በሕዝባዊ ወገንተኝነትና ጀግንነት ለማገልገል ዝግጁ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቃለ-መሃላ ይፈጽማል፡፡

## ፲፭. የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባላት መብቶች

፩/ ማንኛውም መለዮ ለባሽ የኮሚሽኑ አመራር እና ሙያተኛ ወታደራዊ ጥቅማጥቅሞችን ፣ ልዩ ልዩ ክፍያዎችንና አገልግሎቶችን ያገኛል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

፪/ ማንኛውም በአገልግሎት ላይ የሚገኝ ደሞዝተኛ የኮሚሽኑ አመራርና ሙያተኛ የጤና እክል ሲያጋጥመው ለራሱ፣ ለትዳር አጋሩና ከ18 አመት በታች ለሆኑ ልጆቹ በመንግሥት ወጭ ነፃ የህክምና አገልግሎት ያገኛል፤

፫/ ማንኛውም የስምሪት ግዳጅ ላይ የሚገኝ የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል በግዳጅ ላይ ተሳታፊ ሆኖ ጉዳት ሲደርስበት ወይም ህመም ቢያጋጥመዉ በመንግሥት የህክምና ተቋማት ነጻ የህክምና አገልግሎት ያገኛል፤

፬/ ማንኛውም የሚሊሻ አባል በግዳጅ ወቅት ስምሪት ላይ ለቆየባቸው ጊዜያት ማካካሻ የሚሆን ልዩ ልዩ ድጋፎችንና አገልግሎቶችን በሚኖርበት አካባቢ በመንግስት እና ማሕበረሰብ ተሳትፎ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

፭/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል የተሰጠውን ተልዕኮ ወይም ግዳጅ ከመወጣት ጋር በቀጥታ በተያያዘ የወንጀልና የፍትሐብሄር ተጠያቂነት ኮሚሽኑ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የሕግ ድጋፍ እንዲያገኝ ይሠራል፤

፯/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያና የሰላም አስከባሪ ዓመታዊና ልዩ ልዩ ፈቃዶችን የማግኘት መብት አለው፤

፯/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ንዑስ አንቀጽ ፯ የተዘረዘሩ መብቶች ዝርዝር ጉዳይ እንደአግባብነቱ በደንብ ወይም በመመሪያ ይወሰናል፤

፰/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ አባል በስምሪት ላይ እያለ በሚደርስበት የአካል ጉዳት ወይም የህይወት መሰዋትነት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ድጎማዎችንና ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት መብት አለው።

## ፲፯. ስለ ኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪና ሚሊሻ አባላት ግዴታ

ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፤ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል፦

፩/ በማናቸውም ጊዜ ለሕግና ሕገ - መንግሥቱ ተገዥ የመሆን፤

፪/ ሕገ - መንግሥቱንና ሕገ - መንግሥታዊ ሥርዓቱን የማክበር፣ የማስከበር እና ከአደጋ የመጠበቅ፤

፫/ የሃገሪቱን፣ የክልሉንና የኮሚሽኑን ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ሕጋዊ ትዕዛዞች የማክበርና የማስከበር፤

፬/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ ቢያንስ ለሰባት ዓመታት የማገልገል፤

፭/ ኢ - ሰብዓዊ ወይም ክብርን ከሚነካ ማንኛውም ዓይነት ንግግር፣ አያያዝ ወይም ድርጊት ራሱን በማራቅ ተልዕኮዉን በሕግ አግባብ ብቻ የመወጣት፤

፮/ ተግባሩን ሲያከናውን ከማንኛውም ዓይነት ወገንተኝነት ነፃ የመሆን፤

፯/ የክልሉን ሰላም እና ደህንነት ከማረጋገጥ በተጨማሪ በሀገሪቱ በሚፈጠሩ አገራዊ ችግሮች ጥሪ ሲደረግለት ከፌደራል መከላከያ ሰራዊቱ እና ከሌሎች የፀጥታ አካላት ጋር የመሰለፍና ጥቃትን የመከላከል፤

፰/የተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አደጋ ሲያጋጥም ከሌሎች የጸጥታ ተቋማትና ከሚመለከታቸው የመንግሥት የአስተዳደር አካላት ጋር በመቀናጀት ድጋፍ የመስጠት ፤

፱/ ለተልዕኮ ማስፈጸሚያ የተሰጠውን የጦር መሳሪያን ጨምሮ ማንኛውንም ዓይነት ንብረት እና ሌሎች ሎጅስቲክስ ነገሮችን ለተፈቀደለት ዓላማ ብቻ እንዲውል የማድረግ፤

፲/ በመንግሥት የተሰጠውን ማንኛውንም ዓይነት የጦር መሳሪያ ከመሸጥ፣ ከመለወጥ፣ ከማከራየት፣ በትውስት ከመስጠት እና ከማበላሸት መቆጠብና ሌሎች ይህን ፈጽመው ሲገኙ ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ፤

፲፩/ በሥራው ምክንያት የሚያውቃቸውን መንግሥታዊና ተቋማዊ ሚስጥሮች የመጠበቅ፤

፲፪/ በሕግ መሠረት የሚሰጡ ተግባራትን ተቀብሎ የመፈጸም፤ ግዴታ አለበት፡፡

## ፲፯. ስለ አገልግሎት ዘመንና የጡረታ መውጫ ዕድሜ

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ ደመወዝተኛ አመራር ወይም ባለሙያ ከተቀጠረበት ጊዜ ጀምሮ ቢያንስ ለሰባት ዓመት የሚያገለግል ይሆናል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አመራሩ ወይም ባለሙያው የሰባት ዓመት ግዴታውን ሳይጨርስ አቋርጦ ቢወጣ ተቋሙ ለረጅም ጊዜ ሥልጠና ያወጣው ወጪ ታስቦ እንዲመልስ ይደረጋል፤

፫/ በየትኛውም እርከን የሚገኝ የኮሚሽኑ ደመወዝተኛ አመራር፤ ባለሙያና የቀጠና አስተባባሪ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሃምሳ አምስት ዓመት ይሆናል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተመለከተው ቢኖርም ጽሕፈት ቤቱ ለሥራ አስፈላጊ ነው ወይም በቀላሉ ሊተካ አይችልም ብሎ ያመነበትን አመራር ወይም ክፍል ኃላፊ ወይም ባለሙያ ወይም ቀጠና አስተባባሪ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ከሦስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ደመወዝተኛ የኮሚሽኑ አመራር፤ ባለሙያ እና የቀጠና አስተባባሪ ከሃያ አምስት አመት በላይ የአገልግሎት ዘመን ካለው የጡረታ መውጫ ዕድሜው አምስት አመትና በታች ሲቀረው በራሱ ፈቃድ ጡረታ ለመውጣት ሊያመለክት ይችላል፤

፮/ ማንኛውም የሰላም አስከባሪ አባል በሃምሳ ዓመት በክብር እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡ አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል።

፯/ ማንኛውም የሚሊሻ አባል በሀምሳ አምስት ዓመት በክብር እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡ አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል።

## ፲፰. ስለ ካሳ፣ ድጎማና ጡረታ

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ የውል ግዴታ የገባበትን የአገልግሎት ዘመን ጨርሶ ከሥራ ሲሰናበት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ይሰጠዋል፤

፪/ ማንኛውም የኮሚሽኑ መለዮ ለባሽ አመራር ወይም ባለሙያ በታወቀ የጸጥታ ስምሪት ላይ እያለ የተሰዋ እንደሆነ መብቱ በወታደራዊ የጡረታ ሕግ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ ወይም ሰላም አስከባሪ በስምሪት ላይ እያለ ሲሰዋ ሕጋዊ ወራሾቹ የስድስት ወር ደመወዝ  በአንድ ጊዜ የሚከፈላቸውና ደሞዝተኛ የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ዘላቂ የጡረታ መብት የሚከበርለት ይሆናል፤

፬/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ ወይም ሰላም አስከባሪ ወይም የሚሊሻ አባል መንግሥት የሰጠውን ግዳጅ ተቀብሎ ሲፈፅም በደረሰበት ጥቃት ምክንያት ከስድስት ወር በላይ አድራሻው ከጠፋ ሕጋዊ ወራሾቹ ሙሉ በሙሉ የካሳና ድጎማ ተጠቃሚ ይሆናሉ፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም አባል ከስድስት ወር በላይ የቆየው በደረሰበት ጥቃት ምክንያት ባልሆነ ወይም አስገዳጅ ባልሆነ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ ለቤተሰቦቹ የተሰጠው ካሳና ድጎማ የሚመልሱ ይሆናል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

፮/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ ወይም ሰላም አስከባሪ ወይም የሚሊሻ አባል ተቋሙ በሚያዘጋጀው ቅጽ ላይ ሕጋዊ ወራሾቹን እንዲያስመዘግብ ይደረጋል፤ በማንኛውም ምክንያት ህይወቱ ቢያልፍ ሕጋዊ ወራሾቹ የሚመለከተው የሕግ አካል በሚወስነው ውሳኔ መሠረት  ለወራሾች በሕግ የተፈቀዱ ክፍያዎች በቀጥታ እንዲከፈላቸው ይደረጋል፤

፯/ ማንኛውም የኮሚሽኑ ደሞዝተኛ አመራር ወይም ባለሙያ በጸጥታ ስምሪት ላይ እያለ በደረሰበት ከፍተኛ የአካል ጉዳት ምክንያት ራሱን መርዳት የማይችል መሆኑ

በታወቀ የመንግስት የህክምና ተቋም የህክምና ቦርድ ሲረጋገጥ የቦርድ  መብቱ ተከብሮለት ይሰናበታል፤

፰/ ማንኛውም ሰላም አስከባሪ ወይም የሚሊሻ አባል በጸጥታ ስምሪት ላይ እያለ በደረሰበት ከፍተኛ የአካል ጉዳት ምክንያት ራሱን መርዳት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ በመንግሥት በሚቋቋም ማዕከል በዘላቂነት እንዲጦር ይደረጋል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

## ፲፱. አገልግሎት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፤ የሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች አገልግሎቱ ሊቋረጥ ይችላል፦

፩/ በራሱ ጊዜ ሲጠይቅ እና የቅጥር ውል ዘመኑ ሲያበቃ፤

፪/ በሞት ሲለይ፤

፫/ የስንብት ጥያቄ አቅርቦ ስንብቱ ሲጸድቅ፤

፬/ ከባድ ህመም ወይም ጉዳት ደርሶበት ለሚሊሻ ተቋሙ ተልዕኮ ብቁ አለመሆኑ በሐኪሞች ቦርድ ሲረጋገጥ፤

፭/ በዕድሜ ጣሪያ በጡረታ ሲገለል ወይም በክብር ሲሰናበት፤

፮/ በጠላት ተማርኮ ወይም ከጠላት ጋር በተደረገ ዉጊያ ጠፍቶ ለ6 ወራት ያህል ሁኔታዉ ያልታወቀ እንደሆነ ፤

፯/ ኮሚሽኑ የመዋቅር ለውጥ ወይም የአሠራር ማሻሻያ በማድረጉ ምክንያት በሥራው እንዲቀጥል ለማድረግ ሳይቻል ሲቀር፤

፰/ በግዳጅ አፈጻጸም ወይም በዲስፕሊን ጉድለት ለአገልግሎት ብቁ አለመሆኑ በየደረጃው መሰናበቱ ሲረጋገጥ፤

፱/ ከግዳጅ አፈጻጸም ሁኔታ ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ በወንጀል ተከሶ በፍርድ ቤት ውሳኔ ጥፋተኛ ተብሎ ሲወሰን።

## ፳. ስለ ዲስፐሊን ጥፋትና ቅጣት

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተካተቱ ግዴታዎችንና ድንጋጌዎችን የተላለፈ እንደሆነ በኮሚሽኑ የዲሲፐሊን ደንብ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፤

፪/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል በዚህ አዋጅ የተቀመጡ ግዴታዎችን ሳይወጣ የቀረ እንደሆነ እንደ ጥፋቱ ክብደት በዲስፕሊን ተጠያቂ ይሆናል ዝርዝሩ በደንብ ወይም በመመሪያ ይወሰናል፤

፫/ የዲሲፕሊን ጥፋት ደረጃዎችን፣ አይነቶችን አጣርቶ ለውሳኔ የሚያቀርብ የዲስፕሊን አጣሪ ኮሚቴ በሁሉም ደረጃ እንዲቋቋም ይደረጋል፤ ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ፳፩. አቤቱታ ስለማቅረብ

ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ የሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል የአስተዳደር በደል ደርሶብኛል የሚል ቅሬታ ካደረበት ውሳኔ ከሰጠው አካል አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ለሚገኘው ኃላፊ አቤቱታ በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

# ክፍል አራት

# ስለ ኃላፊነት ዕድገት፣ የግዴታ አገልግሎት፣ ስንብት፣ ሜዳይና ምስክር ወረቀት

## ፳፪. ስለ ኃላፊነትና ዕድገት አሰጣጥ

፩/ የኃላፊነት ዕድገት ሲሰጥ ብቃትን ፣ መልካም ሥነ - ምግባርንና አገልግሎትን መሠረት ባደረገ ውድድር ሆኖ ሚዛናዊ እና የሴቶችን ተሳትፎ በሚያረጋግጥ መንገድ ይሆናል

፪/ የኮሚሽኑ ኮሚሽነርና የምክትል ኮሚሽነሮች በርዕሰ መስተዳደሩ ይሾማሉ፤

፫/ በክልል ደረጃ ዋና መምሪያ ኃላፊዎችና ዋና ክፍል ኃላፊዎች በኮሚሽነሩ ይመደባሉ፤

፬/ የዞን መምሪያ ኃላፊዎች በዞን ዋና አስተዳዳሪ ወይም በከተማ አስተዳደር ከንቲባ ታይቶ በኮሚሽኑ ማኔጅመንት ኮሚቴ ተወስኖ ሲቀርብ በቢሮ ኃላፊው ይመደባሉ፤

፭/ የዞን መምሪያ ዋና ክፍል ኃላፊዎች በመምሪያ ማኔጅመንት ኮሚቴ ታይቶ በኮሚሽኑ ማኔጅመንት ኮሚቴ ተወስኖ ይመደባሉ፤

፯/ የወረዳ ሚሊሻ  ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች በወረዳ አስተዳዳሪ ወይም በከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ታይቶ በዞን መምሪያ ማኔጅመንት ኮሚቴ ተወስኖ በኮሚሽኑ ይመደባሉ፤

፯/ የወረዳ ሚሊሻ ጽ/ቤት ክፍል ሃላፊዎች በወረዳው ማኔጅመንት ታይቶ በመምሪያ ማኔጅመንት ኮሚቴ ተወስኖ ይመደባሉ፡፡

፰/ የክልል ፤ የዞን፣ የወረዳና የቀጠና መለዮ ለባሽ የባለሙያዎች ምደባ በምደባ የሚፈጸም  ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፳፫. የግዴታ አገልግሎት

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር  ወይም ባለሙያ ልዩ ስልጠና ወይም ትምህርት ተከታትሎ ከጨረሰ በኋላ በሥልጠና ወይም በትምህርት የቆየበትን ጊዜ የማገልገል ግዴታ አለበት፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪ እና ሚሊሻ አባል በክልሉ ወይም በሀገር ደረጃ በተፈጠረ የጸጥታ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ምክንያት የክተት ወይም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሲታወጅ የማገልገል ግዴታ አለበት፤

፫/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪ እና የሚሊሻ አባል በክልሉ ወይም በፌዴራል መንግሥት ደረጃ በተፈጠረ የጸጥታ መታወክ ወይም በአገር መወረር ወይም በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት የክተት ወይም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በታወጀበት ሁኔታ የሥራ መልቀቂያ ወይም ዝውውር ወይም የዓመት እረፍት ፈቃድ መጠየቅ አይችልም፡፡

## ፳፬. ከሥራ የማሰናበት ውሳኔ

አግባብ ባለው የዲስፕሊን አወሳሰን ሥነ-ሥርዓት ደረጃ አልፎ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ ፬፣ ፯፣ ፰ እና ፱ መሰረት አገልግሎት ሲቋረጥ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው በሚከተለው አግባብ ይሆናል፡-

፩/ የመምሪያ ኃላፊ በዞን አስተዳዳሪ ወይም የከተማ አስተዳደር ከንቲባ አስተያየት ሰጭነት በኮሚሽኑ አቅራቢነት በቢሮ ኃላፊው ይወሰናል፤

፪/ በክልል የዋና መምሪያ ኃላፊዎችና ዋና ክፍል ኃላፊዎች፣ መለዮ ለባሽ ባለሙያዎች በኮሚሽኑ የሚወሰን ይሆናል፤

፫/ የዞን ሚሊሻ መምሪያ ዋና ክፍል ኃላፊዎች እና የወረዳ ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በመምሪያው አቅራቢነት በኮሚሽኑ የሚወሰን ይሆናል፤

፬/ የወረዳ ክፍል ኃላፊዎች በመምሪያው ማኔጅመንት ኮሚቴ ይወሰናል፤

፭/ የቀጠና አስተባባሪና የሰላም አስከባሪ አባላት በወረዳው ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ማኔጅመንት ኮሚቴ የሚወሰን ይሆናል፤

፮/ የሚሊሻ አባላትን በተመለከተ በአባላት አስተያየት ተሰጥቶ የመጨረሻ ውሳኔው በወረዳ ማኔጅመንት የሚሰጥ ይሆናል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

## ፳፭. ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ስለሚደረግ ዝውውር

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራርና ባለሙያ በጸጥታ ስራ ስምሪት ላይ ባለበት የአካል ጉዳት ደርሶበት በተቋሙ ላለመቀጠል አሳማኝ ምክንያቶች ሲያጋጥሙ ኮሚሽኑ ከሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ኀብት ልማት ቢሮ ጋር በመነጋገር በሚመጥነው የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ መሠረት በየትኛውም የመንግስት ተቋም ውስጥ በቋሚነት ወይም በጊዚያዊነት ተዛውሮ እንዲመደብ ሊያደርገው ይችላል፡፡

፪/ ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተዛወረ የኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ መብቱና ግዴታው የተዛወረበት መስሪያ ቤት በሚተዳደርበት ሕግ የሚገዛ ይሆናል፡፡

## ፳፮. የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይና የምስክር ወረቀት

ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ በተሰለፈበት አውደ ውጊያ የዘወትር የጸጥታ ግዳጅ አፈጻጸም ከሚጠይቀው በላይ የሚያኮራ ጀግንነት ለፈጸመ ኮሚሽኑ አመራር ወይም ባለሙያ ወይም ሰላም አስከባሪ ወይም የሚሊሻ አባል ሥራው በሚመጥነው ልክ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሽልማት ወይም የላቀ የሥራ ውጤት የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

## ፳፯. ስለ አገልግሎት ዘመን የምስክር ወረቀትና ማበረታቻ

ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ በዲስፕሊንና በሥራ አፈጻጸም ጉድለት የሌለበት ማንኛውም የኮሚሽኑ አመራር፣ ባለሙያ፣ ሰላም አስከባሪና የሚሊሻ አባል እንደየ አገልግሎት ዘመኑ የሚከተለው የአገልግሎት ዘመን የምስክር ወረቀትና ማበረታቻ የገንዘብ ሽልማት ይሰጠዋል፦

፩/ ከ30 ዓመትና በላይ ላገለገለ የአገልግሎት ዘመን አንደኛ ደረጃ የምስክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት፤

፪/ ከ25 አመት በላይ እስከ 29 ዓመት ላገለገለ የአገልግሎት ዘመን ሁለተኛ ደረጃ የምስክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት፤

፫/ ከ20 አመት በላይ እስከ 24 ዓመት ላገለገለ የአገልግሎት ዘመን ሶስተኛ ደረጃ የምስክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት፤

፬/ ከ15 አመት በላይ እስከ 19 ዓመት ላገለገለ የአገልግሎት ዘመን አራተኛ ደረጃ የምስክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት።

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፳፰. ስለ በጀት

የኮሚሽኑ ዓመታዊ በጀት በክልሉ መንግሥት ይመደባል፡፡

## ፳፱. ስለ ግዥና ንብረት አስተዳደር

፩/ ኮሚሽኑ የትኛዉንም ዓይነት ግዥ በመንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር ሕግጋት መሠረት ይፈጽማል፤

፪/ ኮሚሽኑ የመንግሥትን የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር ሕግጋት የተከተለ መዛግብት ይይዛል።

## ፴. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የተጀመሩ የዲሲፕሊን ጉዳዮች፣ የፍርድ ቤት ክርክሮችና ሌሎች ሂደቶች ጉዳዩ ሲጀመር በነበሩት ሕግጋት መሠረት ተጣርተው እልባት ያገኛሉ።

## ፴፩. ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

፩/ የሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፫/፩ሺ፱፻፹፰ እና ማሻሻያዉ አዋጅ ቁጥር ፹፩/፩ሺ፱፻፺፭ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ ላይ የተደነገገው ቢኖርም የሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፫/፩ሺ፱፻፹፰ እና ማሻሻያዉ አዋጅ ቁጥር ፹፩/፩ሺ፱፻፺፭ መሠረት የወጡ ደንብ እና መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ እና በሌላ ደንብና መመሪያ እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፤

## ፴፪. መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፲፫/፩ሺ፱፻፹፰ እና ማሻሻያው አዋጅ ቁጥር ፹፩/፩ሺ፱፻፺፭ ለክልሉ ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ተሰጥተው የነበሩት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና ለተቋቋመዉ ለክልሉ ሚሊሻ ኮሚሽን ተላልፈዋል፡፡

## ፴፫. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስችል ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፴፬. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ይህን አዋጅና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

## ፴፭. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን-------- ፪ሺ፲፰ ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህርዳር

ቀን ————————/-------/፪ሺ፲፰ ዓ.ም

አረጋ ከበደ ለጋስ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚደንት